# የቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዐት

ለመዳን ፈቃደኛነት ያለው ሰው ኹሉ ይህን በኹሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሃይማኖት ይጠብቅ ዘንድ ይገባዋል። ስለዚህም ደኅንነትን እንዲያገኝ ይህን እምነተ መጠበቅ ያስፈልገዋል።

በኹሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትም፦

አካላትን ሳንደባልቅና ህላዌን ሳንከፍል አንዱን አምላክ በሦስትነት ሦስትነትንም በአንድነት እናመልክ ዘንድ ነው።

አንዱ አካል የአብ ሲኾን፥
ኹለተኛው የወልድ፥
ሦስተኛውም የመንፈስ ቅድስ ነው።
ነገር ግን የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንዲት ናት።
ክብራቸውም የተተካከለ ነው። ግርማቸውም የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናት።

አብ እንዳለ እንዲሁም ወልድ አለ፤ መንፈስ ቅዱስም አለ።

አብ አልተፈጠረም፤
ወልድም አልተፈጠረም፤
መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

አብ አይወሰንም (በማስተዋል ረገድ)፤
ወልድም አይወሰንም፤
መንፈስ ቅዱስም አይወሰንም።

አብ ዘለዓለማዊ ነው።
ወልድም ዘለዓለማዊ ነው።
መንፈስ ቅዱስም ዘለዓለማዊ ነው።
ነገር ግን በዘለዓለማዊነት ያለ አንድ ነው እንጂ ሦስት ናቸው አንልም።

እንዲሁም የማንወስነውና ያልተፈጠረ አንድ ነው እንጂ የማንወስናቸውና ያልተፈጠሩ ሦስት ናቸው አንልም።

እንደዚሁም አብ ኹሉን ቻይ ነው፤
ወልድም ኹሉን ቻይ ነው፤
መንፈስ ቅዱስም ኹሉን ቻይ ነው።
ነገር ግን ኹሉን የሚችል አንድ ነው እንላለን እንጂ ሦስት ኹሉን ቻዮች አንልም።

እንደዚሁም አብ አምላክ ነው፤

ወልድም አምላክ ነው፤
መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው፤
ዳሩ ግን አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አማልክት አንልም።

እንደዚሁም አብ ጌታ ነው፤

ወልድም ጌታ ነው፤
መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው፤
ስለ ኾነም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አንልም።

በክርስትና እውነትነት እንደምንለው፡-

አካል ኹሉ እያንዳንዱ በየራሱ አምላክና ጌታ ሆኖ ሳለ ሦስት አማልክትና ሦስት ጌቶች ከማለት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አምልኮ እምነት ትከለክለናለች።

አብ ከማንም አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደም፤

ወልድም በአብ ነው፤ ስለ ኾነም ተወልዶ ነው እንጂ ተሠርቶ ወይንም ተፈጥሮ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም በአብ ነው። ዳሩ ግን ሠርጸ እንጂ ተሠርቶ ወይንም ተፈጥሮ ወይም ተወልዶ አይደለም።

እንግዲህ አንድ አብ አለ እንጂ ሦስት አባቶች የሉም።
አንድ ልጅ አለ እንጂ ሦስት ልጆች (ወልዶች) የሉም።
አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ እንጂ ሦስት መንፈስ ቅዱሶች የሉም።
በዚችም ሦስትነት መቅደም መከታተል የለም፤ ከባልንጀራውም የሚበልጥና የሚያንስ የለም። ሦስቱ አካላቶቻቸው እየራሳቸው የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናቸው። እየራሳቸውም የተተካከሉ ናቸው። እንግዲያውስ እንደ ተባለው ኹሉ ሥላሴን በአንድነት አንድነትንም በሥላሴ ማመን ይገባል።

መዳንን የሚሻ በሥላሴ እንደዚሁ ያስብ።

ዳግም ስለ ዘለዓለም ሕይወቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትሥጉት በሚገባ ያምን ዘንድ ለሰው ያስፈልገዋል።

ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችን ስትባል ይህንኑ ማመናችን ማለት እንደ መኾንዋ፡-

ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና ሰው ነው። እም ቅድመ ዓለም ከአብ ህላዌ በመወለዱ አምላክ ነው፤ ድኅረ ዓለምም ከእናቱ ህላዌ በመወለዱ ሰው ነው። በሰው ነፍስና ሥጋ ጥዩቅ ሰው ኾኖ ፍጹም አምላክ ነው። በመለኮቱም ከአብ ጋር አንድ ሲኾን የባሪያውን መልክ ወሰደ። ዳሩ ግን አምላክና ሰው እንደ መኾኑ አንድ ክርስቶስ ነው እንጂ እርሱ ኹለት አይደለም። አንድነው፤ ግን መለኮቱ ሰውነትን በመገንዘብ ነው እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ በመለወጥ አይደለም። ፈጽሞ ተዋሐደ፤ ስለ ኾነ በባሕርይ መደባለቅ ሳይኾን በአካል መዋሐድ ነው። ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሚያሰኝ ኹሉ አምላክና ሰው የኾነ አንድ ክርስቶስ ነው።

እርሱም እኛን ለማዳን መከራን ተቀበለ፤ ወደ ሲኦልም ወረደ።
በሦስተኛም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።
ወደ ሰማይም ዐረገ።
ኹሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ።
በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድም ከዚያ ይመለሳል።

እርሱም በሚመጣበት ጊዜ ሰው ኹሉ በሥጋው ይነሣል።
ባደረገውም ሥራ ኹሉ ይቈጣጠረዋል።
መልካም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ክፉ የሠሩም ወደ ዘለዓለም እሳት ይገባሉ።

ከኹሉ በላይ የምትኾን የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ይህች ናት፤ ያላመናት ሰውም ይድን ዘንድ አይቻለውም።

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን፤ በመጀመሪያ እንደ ነበረ አኹንም እንዳለ ለዘወትርም እንደሚኖር ለዘለዓለም አሜን (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ 1951፣ 38-40)።

English Version can be found at: (http://www.crcna.org/welcome/beliefs/creeds/athanasian-creed)

Whoever desires to be saved should above all hold to the catholic faith.

Anyone who does not keep it whole and unbroken will doubtless perish eternally.

Now this is the catholic faith:

That we worship one God in trinity and the trinity in unity,
neither blending their persons
nor dividing their essence.
For the person of the Father is a distinct person,
the person of the Son is another,
and that of the Holy Spirit still another.
But the divinity of the Father, Son, and Holy Spirit is one,
their glory equal, their majesty coeternal.

What quality the Father has, the Son has, and the Holy Spirit has.
The Father is uncreated,
the Son is uncreated,
the Holy Spirit is uncreated.

The Father is immeasurable,
the Son is immeasurable,
the Holy Spirit is immeasurable.

The Father is eternal,
the Son is eternal,
the Holy Spirit is eternal.

And yet there are not three eternal beings;
there is but one eternal being.
So too there are not three uncreated or immeasurable beings;
there is but one uncreated and immeasurable being.

Similarly, the Father is almighty,
the Son is almighty,
the Holy Spirit is almighty.
Yet there are not three almighty beings;
there is but one almighty being.

Thus the Father is God,
the Son is God,
the Holy Spirit is God.
Yet there are not three gods;
there is but one God.

Thus the Father is Lord,
the Son is Lord,
the Holy Spirit is Lord.
Yet there are not three lords;
there is but one Lord.

Just as Christian truth compels us
to confess each person individually
as both God and Lord,
so catholic religion forbids us
to say that there are three gods or lords.

The Father was neither made nor created nor begotten from anyone.
The Son was neither made nor created;
he was begotten from the Father alone.
The Holy Spirit was neither made nor created nor begotten;
he proceeds from the Father and the Son.

Accordingly there is one Father, not three fathers;
there is one Son, not three sons;
there is one Holy Spirit, not three holy spirits.

Nothing in this trinity is before or after,
nothing is greater or smaller;
in their entirety the three persons
are coeternal and coequal with each other.

So in everything, as was said earlier,
we must worship their trinity in their unity
and their unity in their trinity.

Anyone then who desires to be saved
should think thus about the trinity.

But it is necessary for eternal salvation
that one also believe in the incarnation
of our Lord Jesus Christ faithfully.

Now this is the true faith:

That we believe and confess
that our Lord Jesus Christ, God's Son,
is both God and human, equally.

He is God from the essence of the Father,
begotten before time;
and he is human from the essence of his mother,
born in time;

completely God, completely human,
with a rational soul and human flesh;
equal to the Father as regards divinity,
less than the Father as regards humanity.

Although he is God and human,
yet Christ is not two, but one.
He is one, however,
not by his divinity being turned into flesh,
but by God's taking humanity to himself.
He is one,
certainly not by the blending of his essence,
but by the unity of his person.
For just as one human is both rational soul and flesh,
so too the one Christ is both God and human.

He suffered for our salvation;
he descended to hell;
he arose from the dead;
he ascended to heaven;
he is seated at the Father's right hand;
from there he will come to judge the living and the dead.
At his coming all people will arise bodily
and give an accounting of their own deeds.
Those who have done good will enter eternal life,
and those who have done evil will enter eternal fire.

This is the catholic faith:
one cannot be saved without believing it firmly and faithfully.

We grant permission to download for personal use, a ministry setting, or classroom use provided that the material is distributed for free and the copies include this credit line: © 1987, CRC Publications, Grand Rapids MI. www.crcna.org. Reprinted with permission.